በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ

የ6ኛ ክፍል ሞዴል ፈተና

አካባቢ ሳይንስ 2015ዓ.ም/ 2023 እኤአ

የጥያቄ ብዛት: 40 **የተፈቀደው ሰዐት: - 1 ሰዐት**

አጠቃላይ ትዕዛዝ

ይህ **አካባቢ ሳይንስ** ቋንቋ ፈተና ነው። በዚህ ፈተና ውስጥ 40 ጥያቄዎች ተካተዋል፤ ለእያንዳንዱ ጥያቄ ትክክለኛ መልስ የሆነውን አማራጭ የያዘውን ፊደል በመመረጥ ለመልስ መስጫ በተሰጠው ወረቀት ላይ በማጥቆር መልስ ይሰጣል። በፈተና ላይ የተሰጡትን ትእዛዞች በጥንቃቄ በማንበብ ፈተናውን መስራት ይጠበቅባችኋል። መልስ የሚሰጠው ከፈተናው ጋር በተያያዘው የመልስ መስጫ ወረቀት ላይ ነው ፤በመልስ መስጫው ላይ ትክክለኛውን መልስ የሚጠቆረው በእርሳስ ብቻ ነው፤ ትክክለኛው መልስ በማጥቆር ሲሰራ ለማጥቆር የተፈቀደው ቦታ በሙሉ በሚታይ መልኩ በደንብ መጥቆር አለበት፤ የጠቆረውን መልስ ለመቀየር ቢፈለግ በፊት የጠቆረውን በደንብ በማጥፋት መጽዳት አለበት።

ፈተናውን ሰረቶ ለመጨርስ የተፈቀደው ሰአት 1 ሰአት ነው። ፈተናውን ሰርቶ ለመጨረስ የተሰጠው ሰዐት ሲያበቃ ለመስሪያነት የምንጠቀምበትን የመጻፊያ እርሳስ ማስቀመጥ እና ፈተናው መስራት ማቆም አለብን። ፈተናው እንዴት እንደሚሰበሰብ በፈታኙ/ኟ እስከሚነገር ድረስ በቦታችን ተቀምጠን መጠበቅ አለብን።

መኮረጅ ወይም በፈተና ሰአት የፈተናን ህግ የማያከብር ተፈታኝ ፈተናው አይያዝለትም፤ ፈተናውን እንዳይፈተንም ይደረጋል።

ፈተናውን መስራት ከመጀመራቹሁ በፊት በመልስ መስጫው ላይ መሞላት የሚገባውን መረጃ ሁሉ በጥንቃቄ መሞላት አለበት።

ፈተናውን መስራት ጀምሩ ሳይባል መጀመር አይፈቀድም !

1. በስተሰሜንና በስተምሥራቅ አቅጣጫ ኢትዮጵያን የሚያዋስኑ ሀገራትን በቅድመ ተከተል የሚገልጸው የትኛው ነው?

   ሀ. ኤርትራና ኬንያ ለ. ጅቡቲና ኤርትራ ሐ. ኤርትራና ጅቡቲ መ.ኬንያና ኤርትራ

2. ለአዲስ ገቢ ተማሪዎች የትምህርት ቤት አካባቢን በቀላሉ ለማስተዋወቅ የምንጠቀምበት መንገድ የትኛው ነው?

   ሀ. የቦታውን አንጻራዊ መገኛ በመንገር ለ.የቦታውን ፍጹማዊ መገኛ በመንገር

   ሐ. መሠረታዊ አቅጣጫን በመንገር መ. ካርታ እንዲያነቡ በማድረግ


3. የአንድ ቦታን አንጻራዊ መገኛን በቀጥታ ለመግለጽ የማይጠቅመው የትኛው አገላለጽ ነው?

   ሀ. በስተ ቀኝ ለ. ፊት ለፊት ሐ. 15^0 ሰሜን መ. በስተ ግራ

4. መሰረታዊ አቅጣጫ ጠቋሚ የማይመደበው የትኛው ነው?

   ሀ. ደቡብ ለ. ፊት ለፊት ሐ. ምዕራብ መ. ሰሜን

ከጥያቄ 5 እስከ ጥያቄ 6 የቀረቡትን ጥያቄዎች ሥዕል 1 በመመልከት ትክክለኛውን አንጻራዊ መገኛ ግለጹ፡፡



5. በሥዕሉ መካከል ከምትታየው ሴት አንጻር ትምህርት ቤቱ የሚገኝበት አቅጣጫ ምን ይባላል?

ሀ. ሰሜን ለ. ምሥራቅ ሐ. ደቡብ መ. ምዕራብ

6. በሥዕሉ የሚታየው ሆስፒታል ከሴትየዋ በየትኛው አቅጣጫ ይገኛል?

ሀ. በስተ ቀኝ ለ. በስተግራ ሐ. ፊት ለፊት መ. በስተ ኋላ

7. በሥዕሉ የሚታየው የተማሪዎች አውቶብስ ከሴትየዋ በየትኛው አቅጣጫ ይገኛል?

ሀ. በስተሰሜን ለ. በስተምሥራቅ ሐ. በስተደቡብ መ. በስተምዕራብ

8. በሥዕሉ የሚታዩት የጋራ መኖሪያ ቤቶች ከሴትየዋ በየትኛው አቅጣጫ ይገኛሉ?

ሀ. በስተሰሜን ለ. በስተምሥራቅ ሐ. በስተደቡብ መ. በስተምዕራብ

9. ምሥራቅ አፍሪካን የሚያዋስነው ትልቁ ውሃማ አካል የትኛው ነው?

ሀ. ቀይ ባሕር ለ. ዐባይ ሐ. ሕንድ ውቅያኖስ መ. አትላንቲክ ውቅያኖስ

10. የምሥራቅ አፍሪካ ፍጹማዊ መገኛን በትክክል የሚገልጸው የትኛው ነው

ሀ. ከ18^0 ሰሜን እስከ 27^0 ደቡብ ፣ እንዲሁም ከ22^0 ምሥራቅ እስከ 51^0 ምሥራቅ

ለ. ከ 22^0ሰሜን እስከ 51^0ደቡብ ፣ እንዲሁም ከ 18^0 ምሥራቅ እስከ 27^0 ምሥራቅ

ሐ. ከ18^0 ምሥራቅ እስከ 27^0 ምሥራቅ ፣ እንዲሁም ከ22^0 ሰሜን እስከ 51^0 ደቡብ

መ. ከ18^0 ደቡብ እስከ 27^0 ሰሜን ፣ እንዲሁም ከ22^0 ምሥራቅ እስከ 51^0 ምዕራብ

11. ከሚከቱሉት አንዱ የምሥራቅ አፍሪካ ሀገራት አጎራባች ሀገር አይደለም።

ሀ. ደቡብ አፍሪካ ለ. ሱዳን ሐ. ኬንያ መ. ቦትስዋና

12.ስለ ቋሚ መስመሮች ትክክል ያልሆነው የትኛው አረፍተ ነገር ነው?

ሀ. የአንድን ቦታ ፍጹማዊ መገኛን ለማመልከት ይጠቅማሉ።

ለ. በካርታ ላይ ከምሥራቅ ወደ ምዕራብ ወይም ከምዕራብ ወደ ምሥራቅ ይሰመራሉ።

ሐ. በአጠቃላይ 360 ዲግሪ ይለካሉ።

መ. መሬትን በምሥራቅና በምዕራብ ንፍቀ ክበባት ይከፍላሉ።

13.በምሥራቅ አፍሪካ ሀገራት የሚገኘው የኪሊማንጃሮ ተራራ ከፍታው ምን ያህል ነው?

ሀ. 5,200 ሜትር ለ. 5,895 ሜትር ሐ.4,620 ሜትር መ. 4,321 ሜትር

14.በኢትዮጵያ **የማይገኘው** ወንዝ የትኛው ነው?

ሀ. ገናሌ ለ. የሩቩማ ወንዝ ሐ. ዋቢ ሸበሌ መ. ዐባይ

15.ለተሸከርካሪና በራሪ አካላት አቅጣጫ ለመጠቆምና ፍጥነት ለመቆጣጠር የሚያግዘው መሣሪያ ምን ይባላል?

ሀ. ጎግል ካርታ ለ. ጎግል ኧርዝ ሐ. ጂፒኤስ መ. ሁሉም

16. የልብ ተግባር ምንድን ነው?

ሀ. ደም ማጣራት ለ. ደም መርጨት ሐ. ደም ማጠራቀም መ. የደም ሕዋስ መሥራት

17.በሽታን የሚከላከለው የትኛው የደም ክፍል ነው?

ሀ. ፕሌትሌት ለ. ቀይ የደም ሕዋስ ሐ. ፕላዝማ መ. ነጭ የደም ሕዋስ

18. ቀይ የደም ሕዋስ ኦክስጂን እንዲይዝ የሚያስችለው የትኛው ነው?

ሀ. ፕላዝማ ለ. ሄሞግሎቢን ሐ. ፕሌትሌት መ. ነጭ የደም ሕዋስ

19 ደም ሲፈስ በፍጥነት ማቆም የየትኛው የደም ክፍል ተግባር ነው?

ሀ. ፕሌትሌት ለ. ሄሞግሎቢን ሐ. ፕላዝማ መ. ቀይ የደም ሕዋስ

20 ደም ቅዳዎች ወፍራም ግዳግዳ ሊኖራቸው የቻለው ለምንድን ነው?

ሀ. ብዙ ደም እንዲያሳልፉ ለ. የደም ግፊትን እንዲቋቋሙ

ሐ.ብዙ የደም ሕዋሳት እንዲያመርቱ መ. ደም በፍጥነት እንዲያሰራጩ

21 በኦክስጂን የበለፀገ ደም የሚረጨው የትኛው የልብ ክፍል ነው?

ሀ. ቀኝ ተቀባይ ልበ ገንዳ ለ. ግራ ተቀባይ ልበ ገንዳ

ሐ. ቀኝ አቀባይ ልበ ገንዳ መ. ግራ አቀባይ ልበ ገንዳ

22 በጉርምስና ወቅት በወንዶች ላይ የሚታየው ሥነ ሕይወታዊ ለውጥ የትኛው ነው?

ሀ. የቆዳ መለስለስ ለ. የጡት ማጎጥጎጥ ሐ. የድምፅ መጎርነን መ. የዳሌ መስፋት

23 ወር አበባ የሚከሰተው ለምንድን ነው?

ሀ. እንቁላል በእንቁልጢ መፈጠር

ለ. እንቁላሉ ከእንቁልጢ ወደ ማሕፀን ቦይ መግባት

ሐ. የማሕፀን ግድግዳ መፈራረስ

መ. የማሕፀን ግድግዳ በደም ሥርና በሕዋሳት መደራጀት

24 ጸታዊ ጥቃት ምንድን ነው?

ሀ. ጸታን መሠረት ያደረገ የሥራ ክፍፍል

ለ. ሥርዐተ ጸታን መሠረት ያላደረገ የሥራ ክፍፍል

ሐ. በአስገዳጅነት የሚፈጸም የወሲብ ትንኮሳ

መ. ያለ ዕድሜ የሚፈጠር የሥራ ጫና

25 በመቶኛ ሲሰላ ዝቅተኛ ድርሻ ያለው የአየር ምንዝር የትኛው ነው?

ሀ. አርጎን ለ. ኦክስጅን ሐ. ናይትሮጂን መ. ካርቦን ዳይኦክሳይድ

26 የኦክስጅንና የካርቦንዳይኦክሳይድ ልውውጥ የሚደረገው በየትኛው የሥርዓተ ትንፈሳ ክፍል ነው?

ሀ. ትንከረት ለ.ድኅረ-አፍ ሐ. ሰርን መ. ዐቢይ ትንባ

27 በኢምጋት ከሳንባችን መጠኑን ጨምሮ የሚወጣው የትኛው ጋዝ ነው?

ሀ. ኦክስጅን ለ. ካርቦንዳይ ኦክሳይድ ሐ. ናይትሮጅን መ. ሃይድሮጅን

28 በምጋትና በኢምጋት ሂደት ምንም ጥቅም ሳይሰጥ ከሳንባችን የሚወጣው የትኛው ጋዝ ነው?

ሀ. ናይትሮጅን ለ. ካርቦን ክልተኦክሳይድ ሐ. ኦክስጅን መ. ሃይድሮጅን

29 ወደ ሳንባችን የሚገባውን አየር በማሞቅ ቆሻሻንና ጀርምን የሚያጣራው የሥርዓተ ትንፈሳ ክፍል ምን ይባላል?

ሀ. ሰርን ለ. ትንከረት ሐ. ድልሺ መ. ትንሿ

30 ውሕድ ዘር የሚፈጠረው በምን አማካኝነት ነው?

ሀ. በቅልቅል ለ. በኬሚካል አጽግብሮት ሐ. በአካላዊ አድግብሮት መ. በድብልቅ

31 ከሚከተሉት ውስጥ በልይ- ዘር ድብልቅ የሚመደበው የትኛው ነው?

ሀ. የስኳር ሙሙት ለ. ደም ሐ. አየር መ. አልኮሆል

32 ቡናን ለማስከን የሚውለው የልየታ ዘዴ ምን ይባላል?

ሀ. ጥልያ ለ. ንጥረት ሐ.ትነት መ.ቀረራ

33 የምድራችን ዋና የጉልበት ምንጭ የሚገኘው ከምንድን ነው?

ሀ. ነፋስ ለ. ውሃ ሐ. ጸሐይ መ. ነዳጅ

34 ታዳሽ የተፈጥሮ ሀብት የሆነው የትኛው ነው?

ሀ. ብረት ለ. ዕጽዋት ሐ. ወርቅ መ. የተፈጥሮ ጋዝ

35 ታዳሽ ያልሆኑ የተፈጥሮ ሀብት ዋና መገለጫቸው ምንድን ነው?

ሀ. በሁሉም ሥፍራ መገኘታቸው ለ. በቀላሉ ጥቅም ላይ መዋላቸው

ሐ. የሚያልቁ መሆናቸው መ. በዝቅተኛ ዋጋ መገኘታቸው

36 ብርትኳን ለመቁረጥ የሚጠቅመው የትኛው ቀላል መኪና ነው?

ሀ. ሽክርክሪት ለ. ሽብልቅ ሐ. መፈንቅል መ. ዘንባይ ወለል

37 የመፈንቅል ክፍል ያልሆነው የትኛው ነው?

ሀ. ጥረት ለ. ድጋፍ ሐ. በክራ መ. ሽክመት

38 ከከርሠ ምድር ውሃ ለማውጣት የሚያግዘ ቀላል ማሽን ምን ተብሎ ይጠራል?

ሀ. ሽክርክሪት ለ. ሽብልቅ ሐ.መፍቻ መ.ሽክርክሪትና ዘንግ

39 አብዛኛው የምሥራቅ አፍሪካ ሀገራት የተለያየ የሙቀት መጠን የሚታየው በምን ምክንያት ነው?

ሀ. ከምድር ወገብ ባላቸው ርቀት ለ. በከፍታ ልዩነት

ሐ. በደመና ሽፋን ልዩነት መ. ከውቅያኖስ ሞገድ ባላቸው ርቀት

40 በምሥራቅ አፍሪካ ሰሜናዊ ክፍል የሚገኙ ብዙ አካባቢዎች ዝናብ የሚያገኙት በየትኛው ወራት ነው?

ሀ. ከመስከረም እስከ ሰኔ ለ. ከሰኔ እስከ መስከረም

ሐ. ከታኅሣሥ እስከ የካቲት መ. ከጥቅምት እስከ ሚያዝያ